በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 213553

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ አማረ -- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኮልፌ ቅዱስ ራጉኤል አዲስ ህይወት አክስዮን ማህበር -- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ የተወሰነበትን አግባብነት ከመተዳደሪያ ደንባቸውና አግባብነት ካላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች ከሌሎች 16 ሰዎች ጋር በመሆን በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች በቀን 29/12/2011 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ተከሳሽ በ1991 ዓ.ም በተፈረመ እና ሙሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሙሉ በተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 55,200.00 (ሀምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ) በሆነ እንዳንዳቸው ብር 50.00 በሚያወጡ 1104 አክስዮኖች የተመሰረተ ሲሆን ከሳሾች እያንዳንዳችን የተለያዩ ብዛት ያላቸው አክስዮኖች የገዛን እና ሙሉ ክፍያ የፈጸምን የማህበሩ ባለድርሻዎች ነን፡፡ ማህበሩ ከተመሰረተ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜ ያለምንም ድንገተኛ ጉባኤ ውሳኔ ገንዘብ ገቢ እንድናደርግ ተጠይቀን ከሳሾች እያንዳንዳችን ለማህበሩ የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ ገቢ ያደረግን ቢሆንም ገቢ ባደረግነው ገንዘብ ልክ አዲስ የአክስዮን ድርሻ አልተሰጠንም ወይም ባወጣነው ገንዘብ መጠን ልክ ያሉን የአክስዩን ድርሻዎችን ዋጋ እንዲጨመር አልተደረገልንም፡፡ ተከሳሽ በቀን 30/10/2010 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባወጣው ማስታወቂያ ከሳሾች እያንዳንዳችን ከብር 50,000.00 (ሀምሳ ሺህ) በላይ ያልከፈልነው ውዝፍ እዳ ያለብን መሆኑን ገልጾልናል፡፡ ከሳሾች እንዳንሳተፍ በተከለከልንበት እና ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔም ከሳሾች አለባቹ የተባልነውን የሊዝ ክፍያ፣ ውዝፍ የቦታ ኪራይ፣ የግንባታ እና የተለያዩ ውዝፍ ክፍያዎች ከነመቀጫው የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ (እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ) ክፍያውን የማናጠናቅቅ ቢሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት የከሳሾችን ስም በመሰረዝ አክስዩን ማህበሩ ባስገነባነው የገበያ አዳራሽ ህንጻ ውስጥ በከሳሾች ስም የተመዘገቡ ሱቆችን ወደ አክስዩን ማህበሩ የሚጠቃለሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባደረገው ጉባኤ ያሳለፈው ውሳኔም በራሱ ህገወጥ በመሆኑ ፈራሽ ከመሆኑም በላይ የጠቅላላ ጉባኤው ጥሪ የተደረገው የአገልግሎት ግዜያቸውን በጨረሱ የስራ አመራር ቦርድ አባላት በመሆኑ ውሳኔው ፈራሽ ሊደረግ የሚገባ ነው፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ማህበር በቀን 10/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ህገወጥ በመሆኑ እንዲሰረዝ፤ ተከሳሽ በሚያደርጋቸው እና በሚጠራቸው ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ከሳሾች እንድንሳተፍ የሚያደርገው ክልከላ ህገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰን፤ እንዲሁም የተከሳሽ ስራ አመራር ቦርድ የአገልግሎት ዘመኑ አልቋል ተብሎ እንዲወሰንልንና የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ተደርጎ አዲስ የስራ አመራር ቦርድ እንዲመረጥ እንዲወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ ከ1ኛ-12ኛ ከሳሾች (2ኛ ከሳሽ የነበሩትን የአሁን አመልካች ጨምሮ) ከማህበሩ እንዲሰረዙ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰኔ 19/2008 ዓ.ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንጂ ሰኔ 10/2010 ዓ.ም አይደለም፡፡ ሰኔ 10/2010 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ ለፎርማሊቲ ከሌሎች ጋር ስማቸው በመጠቀሱ እንጂ ከሳሾች ቀደም ሲል ተሰርዘዋል፡፡ የተሰረዙበትን ሰኔ 19/2008 ዓ.ም የተደረገውን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለማስፈረስ ከሳሾች በተከሳሽ አክስዬን ማህበር ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ መስርተው ተወስኖባቸው በይግባኝም እስከ ከፍተኛው ፍ/ቤት በመሄድ ክሳቸው ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም፡፡ ማህበሩ በተመሰረተ ግዜ በወቅቱ ህጋዊ እውቅና ለማግኘት ባስመዘገበው ካፒታል ብቻ ለአባላት ጥቅም የሚያስገኝ ግዙፍ ተግባር እሰራለሁ ብሎ ሳይሆን ሰፊ ራዕይ ሰንቆ በመነሳት በግዜያዊነት የያዘውን መሬት በሊዝ በመግዛት ህንጻ ለመገንባት ስለነበር በዚው መሰረት አባላት በየግዜው የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ተገዥ በመሆን በነፍስ ወከፍ ከብር 280,000.00 በላይ መዋጮ እያዋጡ ዛሬ ከብር 360,000,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሚሊየን) በላይ የሚያወጣ ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ህንጻ ተገንብቶ ግዴታቸውን የተወጡት አባላት ተጠቃሚ እየሆኑ ናቸው፡፡ በዚህም ከሳሾች እንደ ሌሎቹ አባላት ግዴታቸውን ሳይወጡና ተሳትፎ ሳያደርጉ በሌላው ድካምና ገንዘብ የተገነባው ህንጻ ባለቤት ለመሆን ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሳሾች እንዲከፍሉ የተጠየቁት ልዩ ልዩ ክፍያዎች በየጊዜው በሚደረገው የአክስዬን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሰረት ሲሆን ሌሎች የማህበሩ አባላት ያወጡትን የግንባታ መዋጮም ሆነ ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎች ላለመክፈል ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ የተከሳሽ ማህበር ቦርድ የምርጫ ጊዜን በተመለከተ የተከሳሽ አክስዬን ማህበር ቦርድ ምርጫ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ጸድቆ የወጣው ጥር 2008 ዓ.ም በመሆኑ እና የ3 አመቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ግዜው የሚያበቃው ጥር 2011 ዓ.ም ስለሆነ የከሳሾች ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከ1-12ኛ ያሉ ከሳሾች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሰኔ 19/2008 ዓ.ም ክፍያ ያልከፈሉ አባላት ከማህበሩ እንዲሰናበቱ ያስተላለፈው ውሳኔ ላይ እንዲሰረዝላቸው በመ/ቁ 246539 ክስ አቅርበው ክሱ በይርጋ ውድቅ የተደረገ እና በይግባኝም በመ/ቁ 193641 የጸና ሲሆን ይህ ውሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታና ከሳሾች ከፍለው የቀረቡ በመሆኑ በማህበር አባልነታቸው እንዲቀጥሉ የተባለበት አግባብ በሌለበት ሁኔታ እንዲሁም ይህ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ውሳኔ መሰረት በአባላት እንዲከፈል ውሳኔ የተሰጠበትን ክፍያ ሌሎች የማህበሩ አባላት ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት መከራከሪያ የሌለ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከሳሾች በጠቅላላ ጉባኤው በሰኔ 19/2008 ዓ.ም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ክፍያ የፈጸሙ ስለመሆኑ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ ከሳሾች ቀሪ የማህበሩ አባላት ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ባደረጉበት አግባብ እንዲሁ በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መከፈል ያለበትን ክፍያ መክፈል ይገባቸው የነበረ ሲሆን ሆኖም እንደ ማህበር አባልነታቸው ይህን ግዴታቸውን እንደ ሌሎች የማህበሩ አባላት ያልተወጡ ሲሆን ሰኔ 30/2010 ዓ.ም በወጣው የጋዜጣ ማስታወቂያም ከ2ኛ ከሳሽ በስተቀር የቀሪ ከሳሾች ስም ተጠቅሶ ቀሪ ክፍያ እንዲፈጽሙ መጠየቁ በጠቅላላ ጉባኤው ያልከፈሉ አባላት እንዲሰናበቱ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም የተከናወነ መሆኑን ከሚያመላክት በስተቀር ከሳሾች በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ክስ በቀረበበት ግዜ እንኳን መክፈል ያለባቸውን ክፍያ ያልከፈሉ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ በሆነበት አግባብ ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባደረገው የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰናበቱ ውሳኔ መስጠቱ በህግ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ከሳሾች አዲስ የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄም የአባልነት መብታቸው ቀሪ በሆነበት ሁኔታ ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 2ኛ ከሳሽ (የአሁን አመልካች) ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 27/12/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተፈጸመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤት በማስረጃ ሳያጣራ ቀድሞ በመ/ቁ 246539 እና በመ/ቁ 193641 ተከራክረውበታል በማለት ብቻ የቀድሞው ክርክር አመልካች ቢያንስ የጋዜጣ ጥሪ መደረጉን ባወቅሁ 3 ወር ባልሞላ ጊዜ (በ26 ቀን ውስጥ) ብር 10000.00 ወደ ማህበሩ ገቢ ያደረኩበትን ማስረጃ እንኳ መመርመር ሲገባው አስቀድሞ በይርጋ በብይን የተዘጋውን መዝገብ ተንተርሶ ውሳኔው አልተለወጠም ሲል መወሰኑ ፤ እንዲሁም ከፍተኛው ፍ/ቤትም ብር 10,000.00 የገባበትን አግባብ አጣራለሁ በማለት ያስቀርባል ካለ በኋላ ውሳኔውን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማጽናቱ ስህተት ነው፤ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በትዕዛዝ እንዲቀርቡልኝ የጠየኳቸውን ማስረጃዎች አስቀርበው አልመረመሩም፤ የቀረቡትንም አላጣራም፤ ተጠሪ የማህበሩ አባል አይደሉም ሲል በግልጽ ክዶ አልተከራከረም፤ ተጠሪ ባመነው መሰረትና በማስረጃነት የጠቀስኳቸውን ምስክሮች ተጣርቶ አለመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት እንዲመለስና እንዲቀርቡ የተጠየቁ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ተሰምተው እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ ከፍሲል በመግቢያችን የገለጽነው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ የስር ክርክሩን በማጠናከር በቀን 30/07/2014 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መተዳደሪያ ደንቡንና ህጉን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ከሰጠ ውሳኔው ሁሉም አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ በጉባኤው ያልነበሩም ሆኑ ተገኝተው በሃሳብ የሚለዩትን ሁሉ ያስገድዳል፡፡ (የንግድ ህጉን አንቀጽ 388(1) እና 416(1) ይመለከቷል)፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በአባልነት ከመመዝገባቸው ባለፈ እንደሌሎች አባላት ለረዥም ዘመን መዋጮ በማዋጣት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ሰኔ 19/2008 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ጉባኤ ከአባልነት እንዲሰረዙ መወሰኑና አመልካችም ይህን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም ለማሰረዝ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 246539 ክስ አቅርበው ውድቅ መደረጉ፤ እንዲሁም ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 193641 ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይህ ውሳኔ ባልተለወጠበት እና ፀንቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች ማህበሩ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ለማሰረዝ፤ በጠቅላላ ጉባኤዎች ለመሳተፍ፤ እንዲሁም የተጠሪ ስራ አመራር ቦርድ የአገልግሎት ዘመኑ አልቋል ተብሎ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲወሰንልንና የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ተደርጎ አዲስ የስራ አመራር ቦርድ እንዲመረጥ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ ይሁንና ከዚህ ታልፎ በተያዘው ጉዳይ በተደረገው ክርክር እንደሌሎች አባላት የሚፈለጉባቸውን ክፍያ አለመፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ በማህበሩ የሚቀጥሉበት ምክንያት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ ታይቶ ተሰጠው ውሳኔ ደግሞ የሚነቀፍበት ምክንያት አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ያዳኘነት ጥያቄ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 266589 በቀን 05/11/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243224 በቀን 09/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም